UNITED NATIONS
HUMAN RIGHTS COUNCIL

በ 52 ኛው የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ስብሰባ ፣ የተባበሩት መንግስታት አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ባለሞያዎች በኢትዮጵያ እና የሊቀመንበሩ መግለጫ

መጋቢት 12 ,2023

አቶ ምሃመድ ኦትማን፣ የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ባለሞያዎች ኮምሽን በኢዮትጵያ ሊቀመንበር

**ክቡር ፕረዝደንት ፣ የተከበራቹ፣ ክቡራን ኣባላት እና ታዛቢዎች**

የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን በኢትዩጵያ ስራዎችን ለምክር ቤቱ ለማብራራት ለዚህ እድል አመሰግናለሁ ። መስከረም 27, 2022 ውሳኔ 51/27 የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ መሰረት በማድረግ አዲስ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ሆኜ አገለግላለሁ። ይህን ዕድል በመጠቀም ተባባሪዎቼ ኮሚሽነሮች ላስተዋውቃቹ እወዳሎ። አቶ ስቲቨን ራትነርን የዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ እና ወይዘሮ ራዲካ ኩማራስዋሚ ከስሪላንካ ናቸው። አባል ሀገራት እንደሚያውቁት፣ ኮሚሽኑ በሁለት መልኩ ሃላፊነት ተሰጥቶታል ፡ ከኅዳር 2013 ጀምሮ ተፈፅሟል የተባለውን አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፣ የሰብአዊነት እና የ ስደተኞች መብት ጥሰቶች መርምሮ ሪፖርት ማድረግ እና የሽግግር ፍትህ በተመለከተ ምክር መስጠት ነው ። የተሰጠንን የስራ ሃላፊነት ላይ ለመስራት ከኢትዩጵያ መንግስትና የ አፍሪካ ሕብረት ከተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች ለማግኘት ጥረናል ።

ኮምሽኑ ባለፈው ዓመት መስከረም ወር ላይ የመጀመሪያውን ሪፖርት ለምክር ቤቱ ካቀረበ በኋላ የኢትዮጵያ ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ ተለውጠዋል። ጥቅምት 23 ፣ የፌደራል መንግስት እና የትግራይ ህዝቦች ነፃነት ግንባር (TPLF) የግጭት ማቆም ስምምነት ተፈራርመዋል። ለሁለት አመት የዘለቀ የትጥቅ ግጭት ለማብቃት የታለመ ስምምነት ሲሆን ፣ ግጭቱም በሰሚናዊ ኢትዮጵያ የሚገኙ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሴቶች፣ ወንዶች እና ልጆች ላይ በትግራይ፣ በአፋር ፣ በአማራ ክልሎች ጉዳት ኣድርሰዎል ።ከዛንግዜ ጀምሮ ክልሎቹ ዘለቄታ ያለው ታላቅ ጉልህ እና የግጭቶች ቅነሳ ለውጥ አሳይተዋል ።

ኮምሽኑ የግጭቶች ማቆም ስምምነትን እና ከዚያ በኋላ ያለውን የአተገባበር ስምምነት በጣም በደስታ ተቀብለዋል ፡ በተለይ የሰብአዊ መብቶች ፣ የሲቢል ማህበረሰብ ጥበቃ ፣ ያለገደብ የሰብአዊ እርዳታ ተደራሽነት እና ተጠያቂነት ስምምነቶችን በደስታ እንቀበላለን ። ኮምሽኑ በሃገርአቀፍ ደረጃ እንደዚህ ያሉ ጥረቶች እንዲቀጥሉ በጉጉት ይጠብቃል።

ስምምነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የፌደራል መንግስት ተከታታይ ስራዎችን ጀምሯል። በአከባቢው ባለቤትነት ወደሚገኝ የሽግግር የፍትህ ሂደት የመጀመሪያ እርምጃን የሚያስኬዱ ጅምሮች፥ ይህ ማለትም በሽግግር የፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ላይ ወቅታዊ ምክክርን ያካትታል። ምንም እንኳን መሻሻልን ለመገምገም ግዜው ገና ቢሆንም, ይህ እና ሥርዓተ-ፆታ አካታች ምላሽ ሰጪ፣ ተጎጂዎችን እና ተረጂዎችን ያማከለ የተጠያቂነት አካሄዶች እውነት የመናገር እና እርቅ ፣ ጥገና እንደዚሁም አስፈላጊ ፖሊሲዎች መንደፍ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ እንዳይከሰቱ ማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

የተከበሩት ፕረስደንት እና ክቡራን

ምንም እንኳን አወንታዊ ለውጦች እና በመጠኑ የተሻሻለ የሰዎች ደህንነት ቢኖርም ፣ ከ ኅዳር 2013 ጀምሮ በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጸሙ ጥሰቶች ክብደት እና መጠን መርሳት የለብንም ። ኅዳር 2013 የጀመረው ግጭት ውስጥ የተሳተፉት ሁሉም አካላት የጦር ወንጀሎች፣ የመብት ጥሰት እና የሰብአዊ መብት ጥሰት የእኛ ሪፖርት ፈፅመዋል ብለው ለማመን ምክንያታዊ የሆኑ ምክንያቶችን አግኝቷል።

ኮምሽኑ የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ የተፈጸሙ ጥሰቶች ፣ በተጨማሪ ከባድ ክሶች እና የመብት ጥሰቶችን ማጣራቱን ቀጥሏል። ለእንደዚህ አይነት ድርጊቶች ገለልተኛ ምርመራ እና ተጠያቂነት አስፈላጊ በመሆኑ አትኩሮት ሰጥቶ ይሰራል። ይህም ፍትህን ማስፈን ብቻ ሳይሆን ለተጎጂዎች ወይም ጥቃት የደረሰባቸው እና ቤተሰቦቻቸው ኮምሽኑ ለመጪ የመብት ጥሰቶች እና አላግባብ በደል እንዳይኖር እንደ መከላከያ ዘዴም ነው።

በአለም አቀፍ ህግ መሰረት የፌደራል መንግስት በግጭቶች ወቅት ለተፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነት የማረጋገጥ ቀዳሚ ሃላፊነት አለበት።. በዚህ ረገድ ፣ ተጠርጣሪዎችን የፍትህ በሚኒስቴሩ እና የኢንተር-ሚኒስቴር ግብረ ኃይል (IMTF). በኩል ጨምሮ ከባድ ወንጀሎችን ፈጽመዋል የተባሉ መርምሮ ለህግ ማቅረብ ተነሳሽነትን እናስተውላለን።

በእነዚህ ጥረቶች ዙሪያ መንግሥት የበለጠ ግልጽነት እንዲኖረው ማረጋገጥ እንጠይቃለን። እንዲሁም በዚህ ረገድ ምክር ለመስጠት ዝግጁ ነን።. በኤርትራ ኃይሎች የተፈፀመ ከባድ ጥሰቶች የተጠያቂነት አቅጣጫ አለመኖሩም ያሳስበናል።

የተከበሩት ፕረስደንት እና ክቡራን

ስለ ስራችን ሁኔታ አጭር ወቅታዊ መረጃ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ ።ጠቅላይ ጉባኤው ለኮምሽኑ  የቀረበው ባጀት አጽድቋል ባሁኑ ወቅት ኣዳዲስ የስራ ባልደረቦች እየተቀላቀሉን ይገኛሉ። ባለፈው ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ከሰጠንበት ጊዜ ጀምሮ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርመራዎች እና ስትራቴጂ፥ የጂኦግራፊያዊ ወሰንን በተመለከተ ለማሳወቅ ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክራችንን ቀጥለናል።, የእኛ ምርመራ በታዎች በትግራይ፣ አፋር፣ አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ተፈጽመዋል የተባሉ ጥሰቶች ። መረጃዎች ስፋትን በተመለከተ፣ በመጀመሪያው ዘገባችን ከተገለጹት ከባድ ወንጀሎች በተጨማሪ በተለይም በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት፣ ጾታዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ የሰብአዊ እርዳታን መከልከል እና ሌሎች የሙብት ጥሰቶችም በማየት ላይ እንገኛለን ። የሰራ ድርሻችን እንደሚጠይቀው የዘፈቀደ እስራት፣ የልጆች መብት መጣስ እና የጥላቻ ንግግር ያሉ ሌሎች ጥሰቶች እንዲሁም  የኤርትራ ሃይሎች በኢትዮጵያ ግዛት ጨምሮ በሁሉም አካላት ተፈጽመዋል የተባሉትን ጥሰቶች እየመረመርን ነው።

እስካሁን ድረስ ቢሮው ከተጎጂዎች፣ ከአደጋ የተረፉ እና ምስክሮች ጋር ጥልቅ ቃለ ምልልስ አድርጓል። ይህ አቀራረብ ክፍት የመረጃ ምንጭ  ምርመራ ፣ በጂኦ ስፓሻል እና በሳተላይት ምስሎች ትንተና ያካተተ ነው። በተጨማሪም የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን በማዋሃድ ላይ ጠንካራ ትኩረት መስጠታችንን እንቀጥላለን። በተጨማሪም በልጆች ላይ የሚፈጠረውን ትውልድ ተሻጋሪ የጦርነት ተጽዕኖ ።

ምንም እንኳን  ለኢትዮጵያ መንግስት ፣ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ብናቀርብም።  የምርመራ ቡድናችን አገር ውስጥ እንዲገባ እስካሁን ድረስ ባለመፍቀዱ እናዝናለን። በዚህም ምክንያት አብዛኛው ስራችን በርቀት እየተካሄደ ነው። መንግስት ከ ኮምሽኑ ጋር ያለመተባበር ውሳኔውን በድጋሚ እንዲያስብበት  እንጠይቃለን። በተመሳሳይ መልኩ ፣ አባል ሀገራት ኮምሽኑ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ እንዲረዱ እናበረታታለን። እንዲሁም የኢትዮጵያ ስደተኞች በማስተናገድ ላይ ወደ ሚገኙ ሃገሮች።

ኮሚሽኑ ከዚህ ምክር ቤት በተሰጠው ሥልጣን መሰረት እውነታውን ማስቀመጥ እና በ ጥሰቶች ዙርያ ያሉ ሁኔታዎች ማረጋገጡን ቀጥሏል ። የተፈፀሙ እና በመካሄድ ላይ ያሉ እንዲሁም ወደ ቀጣይ እና ለወደፊቱ የተጠያቂነት ጥረቶች ለመደገፍ ተደራሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ማስረጃዎችን መሰብሰብ እና ማቀብ።

የሽግግር ፍትህ ሃላፊነታችንን በተመለከተ የፖሊሲ ዝርዝር ማዕቀፉ በቅርበት እየገመገምን ነው። በተለይም ከዓለም አቀፍ እና ከ ክልላዊ ደረጃዎችን ጋር በማስተያየት ። ለኢትዮጵያ መንግስት የባለሙያ እና የቴክኒክ ምክር ለመስጠት ቁርጠኝነትችን በድጋሚ እናሳውቃለን። በተመሳሳይ መልኩ ለብሔራዊ የውይይት ኮሚሽን እና ሌሎች የአገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት።

ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና ከምስራቅ አፍሪካ የክልሉ የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ትብብር ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እንዲሁም መረጃ መጋራት መገናኘታችን ቀጥለናል።በቅርብ ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ እድገትን ለማየት ተስፋ እናደርጋለን። የኢትዮጵያን ሁኔታ ከሚከታተሉ በአፍሪካ ህብረት ውስጥ ካሉ አባል መንግስታት እና ሌሎችም ጋር ተገናኝተናል ።

ክቡር ፕረዚደንት ፣ ክቡራን

በመንግስትና በህወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ፍፃሜ አንድ እርምጃ እንደ መሄድ ጠቃሚ ነው። ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር የተከሰቱትን ጥሰቶች መመርመር ያስፈልጋል ከሰላሙ በፊትም ሆነ ከሰላሙ በኋላ ለሰው ልጅ ሙሉ አክብሮት ያለው ስምምነት ሁሌም አስፈላጊ ነው። ከተጎጂዎች እና ከምስክሮች ጋር ከነበረን ቆይታ የተገኘ አስደናቂ መልእክት ነው። ስለደረሰባቸው ጉዳት የበለጠ ግንዛቤ እንዲሰጥ ያላቸው ፍላጎት እና ታላቅ ጥሪ ዘላቂ ሰላም እና ፍትህ ለማግኘት ነው። ብዙዎች ሰላም እና ፍትህ ሁለት የማይነጣጠሉ ናቸው የሚል ጠንካራ እምነት ይገልጻሉ። እርስ በርስ የሚደጋገፉ ዓላማዎች - አንዱ ከሌላው ውጭ ሊኖር አይችልም - ይህ አቋም ሁለቱም ኮሚሽኑ እና ምክር-ቤቱም ይጋሩታል ።

አንድ ካገሩ ተፍናቅሎ ከአንድ አመት በላይ እስር ላይ የቆየ ወዳገሩ መመለስ የማይችል የነገረን፥

'' ወደ ቀድሞ ህይወቴ መመለስ እፈልጋለሁ፣ ግን መጀመሪያ ሰላም ማየት አለብኝ - ወደ ቤት ለመመለስ ደህና መሆን አለበት፣ አሁን ግን አይደለም። ከሰላም በኋላ ህይወታችንን እንደገና ለመገንባት ድጋፍ - ሰብአዊ እና ሌሎች እርዳታ እንፈልጋለን። ከዚያም ፍትህ እንፈልጋለን።

ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች እንደገና ሊያደርጉት እንዳይችሉ መደረግ አለበት ። በመጨረሻም እንዲታወቅልን ያስፈልገናል። በእኛ ላይ የደረሰውን ዓለም እንዲያውቅ እንፈልጋለን። መረሳት የለብንም ።''

አመሰግናለሁ።